www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ የካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 30
ADDIS ABABA 13th February, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፩/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ኦፖርቹኒቲ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………..…………ገጽ ፲፩ሺ

## Content

Proclamation No.1111/2019

International Development Association Loan Agreement for Financing Economic Opportunities Program Ratification Proclamation ...Page 11,000

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፩/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነትለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ኦፖርቹኒቲ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፶፰ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር (ሃምሳ ስምንት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጁን ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1111/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of Fifty-Eight Million Special Drawing Rights (SDR58,000,000) for Economic Opportunities Program, was signed in Addis Ababa on 29th day of June, 2018;

WHEREAS, the House of Peoples’Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 17th day of January, 2019;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

www.chilot.me



**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ኦፖርቹኒቲ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፩/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጁን ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6292-ET ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶፰ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር (ሃምሳ ስምንት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing Economic Opportunities Program Ratification Proclamation No. 1111/2019".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 6292-ET signed in Addis Ababa on 29th day of June 2018 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan Amount of equivalent to Fifty-Eight Million Special Drawing Rights (SDR58, 000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of February, 2019**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**